የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## አስፍቶ ማየትና አርቆ ማየት ለትግሉ ግብ መምታት ወሳኝ ነው!

የሕወሓት/ኢሕዴግ አምባገነን አገዛዝ የሥልጣን እርካቡን ከያዘ ጀምሮ ለሕዝብ መብት የቆሙ፥ የተከራከሩ፥ ድምፃቸውን ያስሰሙ በርካታ ኢትዮጵያውያን ያለ ፍርድ ተገድለዋል፥ በየእስር ቤቱ ማቅቀዋል፥ ኢሰብአዊ ድርጊትም ተፈጽሞባቸዋል።

ከግንቦት ፺፯ ታሪካዊ ምርጫ ወዲህም የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብለው ድምፃቸውን ያሰሙ የቅንጅት መሪዎች፥ የነፃው ፕሬስ አባላትና ሌሎች የሕዝብ ወገኖች ሥልጣን በያዘው ቡድን ማን አለብኝነት ወደ እስር ቤት ተወርውረው እነሆ በስቃይ ላይ ይገኛሉ። የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገልጋይና ታማኝ የሆነው ፍርድ ቤት ገዥው ቡድን ክስ በመመስረተባቸው በእስር ላይ በሚገኙና ከመታሠር ባመለጡ ወገኖች ላይ "ፍርድ" እንደሚሰጥ መገለጹ የታወቀ ነው። በሕወሓት/ኢሕአዴግ ቁጥጥር ሥር ያለ ገለልተኛ ያልሆነ ፍርድ ቤት የሚበየነው ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ የሚከብድ አይደለም። እንኳን ለዚህን ያህል ጊዜ ለአንዲት ሰከንድ እንኳ መታሠር የሌለባቸው ውድ ዜጎችን በእስር ላይ አቆይቶ ማሰቃየት በራሱ ፍርደ-ገምድልነት ነው፥ ኢሰበአዊ ነው፥ መወገዝዝ ያለበት ከይሲና አሉታዊ ተግባር ነው። በግፍ የታሠሩ ዜጎቻችን አለምንም ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ መፈታት አለባቸው የሚለው የሕዝባችን ድምፅ ባሁኑ ወቅት ጎላ ብሎ የሚሰማ ነው። በአስቸኳይ እንዲፈቱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጠይቃል። ፍትኅ ሊኖር የሚችለው አምባገነን አገዛዝ ተወግዶ፥ የሕዝብ መብት ሲከበር ብቻ ነው። ኢትዮጵያውያን በየእስር ቤቱ የሚማቅቁ የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ድምፅን ማስሰማት፥ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን እየተረዱ የሕዝብን መብት ለማስከበር ትግሉን ማጠናከር አማራጭ የሌለው መሆኑንም ይገነዘባሉ።

ታሪካዊውን የግንቦቱን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተከትሎ በደም ባሕር የዋኘው የሽብር አገዛዝ በአገራችን ከተከሰተ ወዲህ በተቃዋሚነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት ደሞክራሲያዊ ኃይሎች አሁን ለምንገኝበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ቅልበሳው ከቀጠለ የሕዝባችንንም ሆነ የአገራችንን ኅልውና ሊፈታተን ለሚችለው አስከፊ የቀውስ አዙሪት የሚመጥን አፀፋ ሲሰጡ አይታዩም። ከዳር አስከዳር ተቀስቅሶ የኢሕአዴግን አገዛዝ ብርክ ካስያዘ በኋላ አደገኛ የሆነ የመፍዘዝ አዝማሚያ የሚያሳየው የግንቦት ሕዝባዊ ማዕበል በመቀዝቀዝ ሂደት ተጉዞ ከተቀለበሰና ሽንፈት ካጋጠመው በአገራችን ሰላም፥ በአገራችን አንድነትና እንዲሁም በዴሞክራሲ ላይ ለማሰብ እንኳን የሚዘገንኑ መዘዞች እንደሚኖሩት ለመገንዘብ በአገራችን የደረሰውንም ሆነ በሌሎች አገሮች የተሸነፉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን ተመክሮ መመልከቱ በቂ ነው።

ዛሬ የምንገኝኝበት ቀውስ ዘርፈ-ብዙ ቢሆንም ከዚህ ሁሉ አሳሳቢው በዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ጎራ የተሰለፉ ወገኖች ተገናኝተውና መክረው የጋራ ትግል ስትራቴጂ እንዲነድፉ በተደጋጋሚ የተደረጉ ጥሪዎች እስካሁን በተግባር አለመተርጎማቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። የዚህ አሳፋሪና አደገኛ ዳተኝነት አንዱ ምክንያት ሽብረተኛውን መንግሥት ለመታገል ፍላጎቱም ወኔውም ሳያንሳቸው ስለተያዘው ቅልበሳ አሳሳቢነት በቂ ግንዛቤ ከማጣት የተነሳ የጋራ ሳይሆን አንድዮሽ የተናጠል ስትራቴጂ እየቀየሱ ለመታገል የመረጡ ወገኖች በመከተል ላይ ያሉት አካሄድ ሆኖ እናገኘዋለን። ስንት ደምና እንባ ከተገበረበት የትግል ታሪካችን ምንም ትምህርት ያልቀሰመና ለመቅሰምም የማይፈልግ ይኸ አካሂድ ከእይታ ስፋቱም ሆነ ከአርቆ ማየቱ አንፃር እጅግ ውሱን በመሆኑ፥ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች አገራችን ያለችበትን አስከፊ ቀውስ በማስወገድ በኩል ውጤት ሊያስገኝ የሚችል ተመጣጣኝ የአፀፋ ተግባራዊ እርምጃዎች እንዳይወስዱ እያደረገ መሆኑ ከዕለት ዕለት በግልጽ የሚታይ ሐቅ ሆኗል።

በአለንበት ወሳኝና አጣዳፊ ወቅት ይኸ ችግር በይሉኝታም፥ በዝምታም ሆነ በቸልታ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ በመሆኑ ከእነዚህ ወገኖችና ከተከታዮቻቸው ጋራ በጥሞና ተወያይቶ ትግሉ ፈር የሚይዝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መሞከር ጊዜ ማጥፋት ሆኖ መታየት የለበትም። እንዲያውም


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

የሕዝባችንን የነፃነት ቀን ለማፋጠን የሚረዳ ጤናማ አካሄድ ነው፡፡ በዝባዝንኬና እጅ እግር በሌላቸው “ልዩነቶች” ሳይሆን በእይታና ፖለቲካዊ ይዘት ባላቸው ቁም ነገሮች ላይ ፍርጥርጥ አድርጎ መወያየትና መከራከር የተቃዋሚውን ጎራ መከፋፈልና ማዳከም አይደለም፡፡ እንዲያውም በግልፅ አጀንዳና በግልፅ አካሄድ ላይ የተመሠረተና ከብረት የጠነከረ የታጋዮች እንድነት ለመመሥረት የሚረዳ ፍቱን አካሄድ ነው፡፡

ጎብረታችን ኢዴፓጎ የወገናችን ክቡር ደምና እንባ የፈሰሰበትን “የሕዝብ ድምፅ ይከበር” አጀንዳ አንግቦ ለአምባ-ገነኖች ፋታ በሚነሳ መልክ ለትግሉ የጋራ አመራር ለመስጠት እንነሳ እያለ ሲወተውት ከአመት ተኩል በላይ እንዳስቆጠረ ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ የታሰሩ መሪዎችንና ሌሎች የኅሊናና የፖለቲካ እስረኞች ንጹሓን ዜጎችን ለማስፈታት፥ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በሕዝባችን ላይ ያወጀውን የሽብር ጦርነት ለመቋቋምና ለማክሸፍ ብሎም ትግሉን ዳር ከማድረስና ግቡን እንዲመታ ከማድረግ አንፃር ወሳኝ ለሆነው የጋራ ትግል ቅንና አገራዊ ጥሪ የዝሆን ጆሮ ሲሰጡ የቆዩ የአንዳንድ ድርጅቶች ክፍሎች አሁንም ጉዳዩን “ለእኛ ተውት” በማለት በተናጠል ትግሉን ለመምራት ሲባዝኑ ይታያል፡፡ በቅርቡ የኅሊና እስረኞችን ለማስፈታት በሚል ሲደረጉ የነበሩ እንቅስቃሴዎች ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እንደዚህ አይነቱ አካሄድ አገራችን ዛሬ በግንቦት ቅልበሳ ማግስት ያለችበትን አሳሳቢ ሁኔታ ያላጤነ ብቻ ሳይሆን ቅልበሳውን በጋራ ትግላችን ከሕዝባችን ጋር ታግለን ካልተቋቋምነው አገራችን በየካቲት 66 ማግስት ከነበረው ተመሳሳይ የቀውስ አዙሪት ውስጥ አሁንም ልትገባ እንደምትችል ያላገናዘበ አካሄድ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ ወገኖቻችንና በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ኃይሎች የአገራችንን ውስብስብና አስከፊ ችግሮች ለመቋቋምና በመጨረሻም ለማስወገድ “ አስፍቶ ማየት፥ አርቆ ማየት!” ያስፈልጋል እያልን ያለንን አስተሳሰብና አቋም በአጭሩ ለማስቀመጥ እንወዳለን፡፡

ዛሬ በግንቦት ቅልበሳ ማግስት አገራችን ያለችበት ሁኔታ ምን የመስላል? እኛም መላው ዓለምም እንደሚያውቀው ሕዝባችን ታግዬ የተጎናፀፍኩትን ድል ስቀማ ታግዬ አስመልሳለሁ ብሎ በመንቀሳቀሱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ንፁህ ዜጎች በጠራራ ፀሐይ ተረሽነዋል፥ ሌሎች “ቤት ይቁጠራቸው” የሚባሉ በግፍና በገፍ ተገድለው በጅምላ መቃብር ተጥለዋል፥ በብዙ አስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ለእስር ተዳርገዋል፥ የሕዝባችንን ትግል ለማሽመድመድ ሆን ተብሎ በተጠነሰሰ ሴራ መሪዎቹና ተመራጮቹ ከሞቀ ቤታቸው ታፍሰው ወህኒ ተወርውረዋል፥ ከግንቦት በፊት በነበረችው ጭላንጭል የፕሬስ ነፃነት በመጠቀም ሲሰሩ የነበሩት በደርዘን የሚቆጠሩ ጋዜጠኞች ታስረዋል፥ ከእስር የተረፉት ሥራና የኑሮ ዋስትና ተነፍገው ከነቤተሰቦቻቸው ለረሃብና ለችግር ተዳርገዋል፥ ብዙዎችም ቤተሰቦቻቸውን በትነው ለመራር ስደት ተዳርገዋል፡፡ የተያዘው አስከፊ የሆነ የቅልበሳ ሂደት ነውና የኢሕአዴግ መሪዎች የአፈና ውርጅብኝ በእነዚህ “ዓይን በሚስቡ” የግፍ ድርጊቶች የሚወሰን ወይም የሚቆም አይደለም፡፡

በጎብረታችን ሁለተኛ ሸንጎ በትክክል እንደጠቆምነው ሥር እየሰደደ ያለው የሽብር አገዛዝ ነውና ዛሬ ዓይን ከሚስበው የከተማ ኃይሎች አፈና በማያንስና እንዲያውም ከዚያ በሚከፋ ሁኔታ በመላ አገሪቱ በፖለቲካ ድርጅቶች አባላት ላይ ብቻ ሳይሆን “ ያኔ በምርጫው ጊዜ ይኸንን ወይም ያንን ተቃዋሚ ኃይል ደግፈሃል፥ ለዚህ ወይም ለዚያ ተቃዋሚ ኃይል ድምፅ ሰጥተሃል፥ ወዘተ…” እየተባሉ ገበሬዎች፥ ሠራተኞች፥ ወጣቶች፥ ሴቶችና ሌሎች ዜጎች በጨካኝ የኢሕአዴግ ካድሬዎችና ሹማምንት ባዕድ እንኳ ያደርገዋል ተብሎ የማይገመት ግፍ እየተፈጸመባቸው ነው፡፡ በአለፈው ወር የወጣው ሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለው ዓለም-አቀፋዊ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት መግለጫ ይኸኑ ያረጋግጣል፡፡ ድርጅቱ በመግለጫው “ትኩረቶች አዲስ አበባ ላይ ቢሆኑም” ከዋና ከተማዋ ውጭ ስለሚካሄደው አፈና ሲያትት በኦሮሞ ክልል የኦነግና የኦብኮ ደጋፊዎች በመባል አሁንም ዜጎች እንዴት እንደሚታፈሱ፥ በአማራው ክልል የተቃወሚ ደጋፊ ወይም “አላስተማማኝ” እየተባሉ ገበሬዎች እንዴት ማደበሪያ እንደሚከለከሉ፥ እንዴት ከመሬታቸው እንደሚነቀሉ፥ እንዴት በውድቅት ሌሊት ቤታቸው እየተሰበረ እንደሚገረፉ ወይም ለእስር እንደሚዳረጉ በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ይኸ በመላ አገሪቱ የሚንፀባረቅ አስከፊ ክስተት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡
ከዚህ ተነስተን ነው ዛሬ በአገር-ወዳዱና በዴሞክራቱ ጎራ ተሰልፈን ለዚች አገር ደኅነነት በመዋደቅ ላይ ያለን ዜጎች ላለንበት ሁኔታ የሚመጥን አፀፋ ለመስጠት እንድንችል መጀመሪያ አስፍተን እንይ የምንለው፡፡ አስፍተን እንይ ስንል ምን ማለታችን ነው?

አስፍተን እንይ ስንል መጀመሪያ የግንቦትን ድል ባለቤትና የቅልበሳውን ሰለባዎች ማንነት በሚገባ እንወቅ ማለታችን ነው:: በግንቦቱ ምርጫ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ድምፃቸውንና አመኔታቸውን የሰጧቸው ድርጅቶች እንደነበሩ አይካድም:: ነገር ግን እኛ ነገሩን አስፍተን የምናይ ኃይሎች በዚያን ወቅት ተገኝቶ የነበረውን ድል የአንድ ወይም ሁለት ድርጅቶች ድል ብቻ አድርገን አናየውም:: ይኽ ድል ከሁሉም በላይ የሕዝባችንና የዴሞክራሲ ድል ነበር ብለን እናምናለን:: በአሁኑ ወቅት በሽብር የተሞላውን የቅልበሳ መዘዝ ገፈት ማን እየተጋተ ነው? ለሚለው ተጨባጭ ጥያቄ መልሳችን እገሌ ከእገሌ ሳይባል ድል አድራጊ የነበረው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው የሚል ነው:: የግንቦት ድል የሚሊዮኖች ድል እንደመሆኑ መጠን ሽንፈትና ቅልበሳ ሲመጣ ደግሞ የዚህን መዘዝ ገፈት የሚቀምሱት እነዚሁ ሚሊዮኖች ይሆናሉ ስንል የየካቲትም ሆነ የሌሎች በሌላው ዓለም የተሸነፉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች እጣ ባሳዩት አሳዛኝ የታሪክ ሐቅ ብቻ ተመርኩዘን አይደለም:: ዛሬ በግንቦት ማግስት የምናየው ይኽንኑ መራራ ሐቅ ነው :: ቅልበሳው በአገር የመጣ በመሆኑ አስፍቶ ማየት ስንል ቅልበሳውን ለመቋቋም የቅልበሳውን መዘዝ ገፈት በመቅመስ ላይ ያለው ዜጋ በሙሉ በአንድነት እንደ አንድ ሰው የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል ማለት ነው::

ሁለተኛ አስፍቶ ማየት ማለት ዛሬ በአገራችን በመውረድ ላይ ያለው የአፈና ውርጅብኝ መሠረታዊ ምንጩ ይኽ የተያዘው የቅልበሳ ሂደት ስለሆነ አፈናው እንዲቆም፥ መሪዎቻቸን እንዲፈቱ እያልን የምናካሂደውን ተገቢ ተጋድሎ ለአንዲት ሰከንድ እንኳን ቢሆን የግንቦትን ድሎች ለማስመለስና የተኮላሸውን የዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) ሂደት <u>መልሶ በእግሩ ለማቆም</u> ከሚደረገው ሕዝባዊ ተጋድሎ ነጥለን ማየት አንችልም ማለት ነው:: ትግላችን በዚህ ሰፊ በሆነ ሕዝባዊ ዓላማ ተንቀሳቀስቅሶ የኢሕአዴግን መንግሥት እንዲያፈገፍግ የሚያስገድድበት ደረጃ ላይ ካልደረሰ ለእስር የተዳረጉትን ወገኖቻችን ማስፈታትም ሆነ የተነጠቁ መብቶቹን ማስመለስ ቀርቶ በሕዝባችን ላይ የሚዘንበውን የቀጣይ የአፈና ውርጅብኝ የምናቆምበት ምንም ተአምር አይኖርም ማለት ነው::

ሦስተኛ አስፍቶ ማየት ማለት የግንቦትን ድሎች ለማስመለስ በሚለው ጉዳይ ላይ የጋራ ግንዛቤ ከተደረሰ ይኽ ድል የሚሊዮኖች እንደመሆኑ መጠን ተመልሶ የሚገኘው በሚሊዮኖች ትግል ብቻ እንጂ በጥቂት “ ግንባር ቀደም” ነን ባዮች ግርግር ወይም በዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብ የተናጠል ግፊት ጨርሶ እንደማይሆን መገንዘብ ያስፈልጋል ማለት ነው:: ሚሊዮኖችን እንደ አንድ ሰው ተንቀሳቅሳቅሳችሁ ጭቆናን ተቋቋሙ፥ ድላችሁን አስመልሱ እያልን ጥሪ እያደረግን አንዳንድ ድርጅቶች እንደሚገፉው “እንደ አንድ ሰው ግን በኛ ሥር ተነስ” ከሚለው አደገኛና ዞሮ ዞሮ ደግሞ ተወደደም ተጠላም በማወቅም ሆነ ለፖለቲካው አዲስ በመሆን ወይም አስፍቶ ካለማየት የትግሉን አንድነት በማስተጓጎል በቀጥታ የኢሕአዴግ ፀረ ሕዝቦች ከሚያደርጉት ተግባር ጋር ተመሳሳይነት ካለው አደገኛ አካሄድ መጠንቀቅና መቆጠብ ያስፈልጋል:: ከዚህ ይልቅ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈው ሁሉ፥ ግምባር ቀደም ነኝ ብሎ “እጅ ለእጅ ተያይዘን እንታገል” ብሎ የሚቀጣጠበውም ሆነ ሁኔታውን በዝምታና በመገረም የሚመለከተው ወይም ብቻየን እወጣዋለሁ ብሎ በስንጥር ለመጓዝ የሚቃጣው ወገን ሁሉ መጀመሪያ ራሱ በአንድነት ቆሞ አርአያነቱን ማሳየት ያስፈልገዋል ማለት ነው::

ይኽ ካልሆነ በእኛ እምነት አንድም በእሳት መጫዎት ነው አንድም በሕዝብ ሰቆቃ መቀለድ ነው:: የሕዝብ ትግል በአምባ-ገነኖች ሲቀለበስና ድሉ ሲነጠቅ በአገር ሰላም፥ ዴሞክራሲና አንድነት ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ጫናና መዘዝ ከሌላው አገርና ሕዝብ ቀርቶ ከራሳችን ልምድ ተነስተን ሁኔታውን በጥሞናና በተገቢ አገናዝቦ፥ ምላሹም እንዲሁ የሰከነና አርቆ ያየ፥ በጠና መሠረት ላይ የተጣለ፥ የተባበረና የተሳሰረ የጋራ ትግል ሊሆን ይገባል እንላለን:: ከዚህ በፊት ከቀሰምነውና ማንም ዛሬ በትገል ላይ “አለሁ” የሚል ኃይል ሁሉ መቅስም አለበት ከምንለው መራራ ትምህርት ስንነሳ ማስተላለፍ የምንፈልገው አንድ መልእክት ብቻ ነው፤ ትግላችን የቅልበሳውን ሂደት ሊያከሽፍ በሚችል አንድና አንድ ብቻ በሆነ <u>የጋራ ትግል</u> መንገድ ካልተጓዝን እኛም አገራችንም፥ ሕዝባችንም ወደ ጥፋት እየሄድን መሆናችንን ነው::

በዚሁ ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ሁሉም ራሱን መጠየቅ ያለበት አንድ መሠረታዊ ጥያቄ አለ:: ይኸውም ሕዝባችን በጋራ ተንቀሰቃሶ ቅልበሳውን በጊዜ ካላቆመው የኢሕአዴግ መሪዎች ምን ገዷቸውና ማን አስገድዷቸው ነው የተያያዙትን የቅልበሳና የጥፋት ፋይል የሚዘጉት? የሚለው ጥያቄ ነው:: በአጓጉልና አደገኛ የህልም ዓለም ውስጥ ስለማንኖር ለዚህ የምንሰጠው መልስ አጭርና ዘግናኝ ነው:: ማንም አያቆማቸውም፥ ይቀጥሉበታል:: ይኽንን ካልን ደግሞ ሕዝባዊ ትግል

በኢሕአዴግ ሽብር ብቻ ሳይሆን በመራር ክፍተትና ዝርክርክነት ከተኮላሸ አገራችን የዛሬ ዓመት÷ የዛሬ ሁለት ዓመትም ሆነ የዛሬ አምስትም አስርም ዓመት የት ነች? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። አርቆ ማየት የምንለው የግል ስትራቴጂያችንን ስንቅይስ ዛሬ ከዓይናችን ሥር ከምናየው አስከፊ ክስተት ብቻ ሳይሆን "ሁኔታው ከቀጠለ ወዴት ያመራል?" ከሚለውም ስሌት መነሳትም እንዳለብንም ለመጠቆም ነው።

ምርጫ በራሱ የፖለቲካ ፕሮግራም አይደለም። ቅንጅትም ሆነ ኢዴኃኅ በግንቦት ምርጫ ሲሳተፉ አገራችን ፊት ለተደቀኑ ከባድ ከባድና የሰማይ ስባሪ ለሚያክሉ "ኢትዮጵያችንን እንደ አገር÷ ሕዝባችንን እንደ ሰብአዊ ፍጡር" ኅልውናቸውን ለሚፈታተኑና ዙሪያ-ገጠም ለሆኑ የኤኮኖሚ÷ የማኅበራዊ ÷ የአካባቢ ቀውሶች÷ ወዘተ... የፖሊሲ አማራጮች አንግበው እንደነበረ ይታወቃል። መናጢ ድህነትም ሆነ የጅምላ ሥራ አጥነት÷ ዘመን አመጣሹ ኤች አይቪ- ኤድስም ሆነ ሌሎች ሳይንስ ሊረሳቸው የቃጣቸው የብሉይ ዘመን በሽታዎች÷ የአካባቢ ውድመትም ሆነ ትውልድ ገዳይ ብለን የፈረጅነው የኢሕአዴግ የትምህርት ፖሊሲ ወዘተ... እየተጋገዙና አንዱ "የሌላው መነሾና ውጤት እየሆኑ" ወደ ጥፋት እየሄድን ነው ብለን በዴሞክራሲያዊና አገራዊ ፖሊሲዎቻችን ዙሪያ ሕዝባችንን ቀስቅሰናል። የኢሕአዴግ መንግሥት "አሸነፍኩ" ሲል በአንድ መልኩ እነዚህን (ዛሬ ባለው ወከባ ምክንያት በተቃዋሚው ጎራ ማንም የማያነሳቸውን) አጥፊ ፖሊዎች እገፋባቸዋለሁ ማለቱ እንደሆነ ግልፅ ነው። ነገ የኢሕአዴግ መሪዎች በአንድ በኩል ኅብረተሰባችንን በሽብር ስላንበረከኩና በሌላ በኩል ደግሞ በባእድ አሳዳሪዎች ፊት ላለመጋለጥ ሲሉ ብቻ እያካሂዱ ያሉትን የአፈና ውርጅብኝ ዓይን በሚስብ መልኩ ሊያረግቡ ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህ አገር-ገዳይ ፖሊሲዎች ስለሚቀጥሉ የኢትየጵያችን የመከራ ዘመን ተባብሶ እንደሚቀጥል ለመተንበይ ጠንቋይ መቀለብ የሚያስፈልግ አይመስለንም።

ከዚህ አስከፊ መፃኢ ዕድል አንፃር አርቆ ማየት ማለት አገራችን ልክ እንደ የካቲት ማግስት ለማሰላሰል እንኳን የሚቀፉ የቀውሶች አዙሪት ውስጥ እየገባች እንደሆነ መገንዘብና ለዚህ ሁኔታ ለሚመጥን ተጋድሎ ራስን ማዘጋጀት ማለት ነው። ይኽን ስንል ደግሞ አንደኛ ለሕዝባችን ቆመናል የሚሉ ኃይሎች ጠባብና ውሱን ከሆነና እንዲሁም እየገባንበት ካለነው ቀውስ አንፃር ሲታይ "እዚህ ግባ" ሊባል ከማይችል የቡድንም ሆነ ድርጅታዊ አጀንዳ ተቆጥበው ቅልበሳውን በጋራ ተጋድሎ ለማክሸፍ ይነሳሱ÷ ሁለተኛ አገራችንና ሕዝባችን ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን ዘግናኝ ቀውሶች ለመቋቋም ትግላቸውን "ይቻላል" በሚል ዘይቤ ብቻ ሳይሆን "ምርጫ የለም! መቻል አለበት!" በሚል ፅናትና ቁርጠኝነት ይያያዙት÷ ሦስተኛ ይኽን ትግል "ብሩኅ ተስፋን" እውን ለማድረግ በሚል የነገ ቅንጦት በሚሻ መንፈስ ብቻ ሳይሆን እናት አገራችንና ይኽን ሰማዕት ሕዝባችንን ከአይቀሬና አስከፊ ጥፋት ለማትረፍ በሚል አልሞት ባይ ተጋዳይነት ብቻ ሊሰጠው በሚችለው ጉልበት÷ ድፍረትና ፅናት ይዋደቁ ማለታችን ነው።

አርቆ ማየት ማለት ቅልበሳውን በዚህ መልክ ታግለን በጊዜ ካላስወገድነው አገራችን አስከፊ የሆነ የቀውስ አዙሪት ውስጥ ትገባለች ማለት ብቻ አይደለም። ትግላችን ከጊዜ ጋር÷ ከዕለት ዕለት የአቀበት ጉዞ የሚሆንበት አደጋ እንዳለም መገንዘብ ይኖርብናል። ቀውሱ÷ ወከባው÷ ቅልበሳው እየከፋ በሄደ ቁጥር የጋራ አማራጭና አመራር በሌለበት ሁኔታ ይኸ ብቻውን ውጤት ያስገኛል ብሎ ማሰብ ህልም ነው። እርግጥ ስለ ወከባውና ስለ ቀውሱ ክፋት የዚህ ሁሉ ገፈት ቀማሽ ለሆነው ሕዝባችን ለቀባሪ ለማርዳት በሆኑ ፋይዳ ቢስ መግለጫዎች የኢሕአዴግን መሪዎች ግፍ "እያጋለጥን" መቀጠል እንችላለን። ይኸ ግን ውጤት ይኖረዋል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በወቅቱ ያልተገቱ ቅልበሳዎች ከባድ ከባድ የአኮኖሚ÷ የማኅበራዊና የፖለቲካ ቀውሶች በማዝነብ ብቻ አይወሰኑም ። ቀውሱ በከፋ ቁጥር በወከባና በሽብር አንገቱን በደፋና በአመራር መዝረክረክ ግራ በተጋባ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚሰፍነው ጨለምተኛነት የኅብረተሰቡን የመቋቋም አቅም እንደሚያሟሽሸውም ትላንትና የየካቲት ማግስት አሳይቶናል÷ ዛሬም በግንቦት ማግስት ይኸው ዳርዳር ማለት የጀመረ መሆኑንና ትግሉም ትጥቁን የመፍታት አደጋ ከፊታችን እንደተደቀነ ጠንቅቆ መገንዘብ ያስፈልጋግል።

በግንቦት የታየውን የሕዝብ ንቃትና የትግል ወኔ እንደ "ዘለዓለማዊ ግኝት" በመውሰድ ችግር ሳይደርስበት ሳይታፈን ለምኔውም ተጠናክሮ ሊቆይ ይችላል እያለ ከሚግደረደር አስተሳሰብ መቆጠብ ያስፈልጋል። ኢሕአዴግ በአመፅ ሊደመስሰው የተነሳውንና ከጦር በላይ የሚፈራውን ይኽን የሕዝብ የትግል ወኔ እኛ ደግሞ ባለማወቅ እየተፈታተንን እንዳናከስመው ከፈለግን ብዙ አማራጭ የለንም። በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፍን ድርጅቶች ሕዝብን ግራ ከሚያጋባና "ሁሉም

አይረቡም” ወደ ሚል ድምዳሜ ከሚገፋፋ ማንኛውም የተናጠል እርምጃና ድርጊት ተቆጥበን፥ ትግሉ ከጊዜም ጋር እንደሆነ ጠንቅቀን በመረዳት ዳተኝነትን አሽቀንጥረን ጥለን በሕዝባችን ፊት እጅ ለእጅ ተያይዘን አርአያነት ያለው የጋራ ትግል ማካሄድ ይጠበቅብናል።

ስለሆነም፤

1. ኢሕአዴግ በግፍ ያሰራቸውን የኅሊናና የፖለቲካ እስረኞችን በተመለከተ ማንኛውም ወገን ሊተባበርበትና ሊረባረብበት የሚገባ የጋራ ጉዳይ አድርጎ ነው ኅብረታችን የሚያየው። ስለሆነም የፖለቲካ ድርጅቶች፥ ከፖለቲካ ድርጅቶችም የተወሰኑ ድርጅቶች የግል ጉዳይ አድርጎ አይቆጥረውም። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከኢትዮጵያዊም አልፎ ማንም ሰብዓዊ ተፈጥሮ ያለው ሁሉ ሊተባበርበት የሚገባ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ጥያቄ ነውና እስረኞቻችንን የማስፈታቱ አጣዳፊና አንገብጋቢ ጉዳይ በተደራጀና ቀጣይነት ባለው መልክ እንቅስቃሴ መደረግ እንዳለበት ያምናል። በእስር ላይ ከሚገኙ የኅሊናና የፖለቲካ እስረኞች በተጨማሪ ኢሕአዴግ የወንጀል እጁን ሊያሳርፍባቸው ያልቻለ ሦስት የኅብረቱ ከፍተኛ አመራር አባላት፥ አቶ ፋሲካ በለጠ፥ አቶ አረጋዊ በርሄና ዶ/ር ነገደ ጎበዜ ላይ በማያውቁትና በማያገባቸው በሌሉበት በፍርድ ስም የአቶ መለስ ዜናዊ አሽባሪ አምባ-ገነን አገዛዝ ከሁሉም ቀን መርጦ በሰማዕታት ቀን የካቲት ፲፪ ፍርደ-ገምድል የፖለቲካ ብይን ለመስጠት እንደተዘጋጀ ይታወቃል። ብይኑ ምንም ይሁን ምን ፍትኅ የጎደለውና በፖለቲካ ስሊት ታጅቦ የሕዝቡን ትግል ለማዘናጋትና ለማሽመድመድ እንደሆነ ግልጽ ነው። በእኛ እምነት “በምኅረት” የሚፈቱ እንኳ ቢኖሩ ነፃ ናቸው ማለት አይቻልም። ልክ እንደ አቶ ስዬ አብርሃ ወይም እንደ አቶ አበራ የማነአብ ፍርድ ቤት “ነፃ” ከለቀቀ በኋላ መልሶ ማጎርና ማሰቃየት በእጃቸው ነው። የሕግ-የበላይነት በሌለበት ሁኔታ ደግሞ ይኸ ክስተት የሚጠበቅ ነው። እንኳን የሕዝብ ተመራጮች ማንም ሰው ያለ ኃጢአቱ በግፍ ሲታሰር የታሰረው ያ ግለሰብ በተናጠል ሳይሆን እስረኛው ፍትኅ ነውና ሁሉም እንደታሰረ መቆጠር አለበት። ስለዚህ ምንም እንኳ የማይጠበቅ ባይሆንም ኢሕአዴግ ካሰራቸው ውስጥ አብዛኞቹን ቢፈታም እንኳ የኢሕአዴግ እስር ቤቶች ከንጹኃን ዜጎች ማጎሪያነት እስከሚፀዱና እስከሚዘጉ ድረስ ትግሉ መቀጠል ይኖርበታል። አሁንም ቢሆን በኅብረቱ እምነት ከሰባት ወራት በፊት ጀምረን እንዳሳሰብነው ሁሉ በኢሕአዴግ የፈጠራ ክስ በግፍ የታሰሩ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና የነፃው ፕረስ አባላትን፥ በአጠቃላይ የኅሊናና የፖለቲካ እስረኞችን ለማስፈታት የሚደረገውን ጥረት በዓለም-አቀፍ ደረጃ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ለማቀናበርና የተባበረና ቀጣይነት ያለው እንቅስቃሴ እንዲደረግ ከሰብኣዊ መብት ተሚጋቾች (ከኢሰመጉ)፥ ከታሰሩ ቤተሰቦች፥ ከሙያ ማኅበራት፥ ከሴቶች፥ ከወጣቶች፥ ከአገር ሽማግሌዎች፥ ከሕግ ባለሙያዎች፥ ከፖለቲካ ድርጅቶች፥ ወዘተ.. የተውጣጣ አንድ “ዜጎች ለኅሊናና ፖለቲካ እስረኞች” ግብረ-ኃይል በአስቸኳይ እንዲቋቋምና በአዲስ መንፈስና የተጠናከረ ዘመቻ እንዲደረግ በድጋሜ ጥሪ እናቀርባለን።

2. ቅድመ-ምርጫ የተቃዋሚው ጎራ በአንድ ወገን ተሰልፎ ምርጫው ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን ዓለም-አቀፍ መስፈርቶች እንዲሟሉ በጋራ እንዲቆም ከሚለው ጀምሮ ከአገዛዙ ጋር የተደረጉ ድኅረ-ምርጫ ድርድሮች በጋራና በሕዝብ ትግል እንዲታጀብ ለማድረግ፥ የጋራ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት ስለማቋቋም ሆነ የሕዝባችንን የተሰረቀ ድምፅ ለማስመለስና ድሉን ለማስጠበቅ፥ ኢሕአዴግ በሕዝባችን ላይ ያወጀውን የሽብር ጦርነት ለመቋቋምና የሕዝቡን ትግል ከቅልበሳ ለማዳን፥ ወዘተ... የጋራ ትግል እንዲካሄድ ኅብረቱ በተደጋጋሚ ጥሪ አድርጓል፥ የጋራውን ትግል እውን ሊያደርጉ፥ ትግሉን ሊያጠናክሩ የሚችሉ መሠረታዊ ሀሳቦችን በየጊዜውና በየሁኔታው አቅርቧል። ጥሪውና ጥረቱ እስካሁን ያሰበውንና የጠበቀውን ፍሬ ያስገኘ ባይሆንም ሕዝባችን የተቀዳጀውን ድል ከቅልበሳ ለማዳን ከጋራ ትግል ውጭ አማራጭ ስለሌለ ኅብረቱ ተስፋ ሳይቆርጥ ይኸ እውን የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች የበኩሉን አስተዋጽዖ እያደረገ ነው። በቅርቡ በጋራ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ከአንጋፋዎቹ የሲቪክ ማኅበራት መሪዎች ለዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ለቀረበው ጥሪ ኅብረቱ አዎንታዊ መልስ የሰጠው ኅብረቱ ከዚሁ በጋራ ትግል ላይ ካለው መተክላዊ እምነትና ፍላጎት በመነሳት ነው። በዚህ ረገድ ይኸ ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት የቀረበን ጥሪ ሁሉም ድርጅቶችና ወገኖች በቀና መንፈስ ተቀብለው ለተግባራዊነቱ ጥረት እንዲያደርጉ እንጠይቃለን።

3. የሕዝባችንን መስዋዕትነት የሚመጥንና ውጤት ያለው ትግል ከማድረግ አኳያ በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶች ከፍተኛ ኃላፊነት አለብን። በቅድመ ዩትሬክት ስብሰባና ከዚያም ወዲህ ስናሳስብ እንደነበረው ሁሉ፥ የኢሕአዴግን አሸባሪ አምባ-ገነን አገዛዝ አፍራሽ እርምጃዎች ገትቶና አስቁሞ፥ ቅልበሳን ተቋቁሞ፥ ለሕዝባችንና ለአገራችን በእርቅና ሰላም ላይ የተመሠረተ

ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለማጎናጸፍ በቅድሚያ የተቃዋሚው ጎራ ሁሉን-አቀፍና አገር-አቀፍ ጉባዔ በአስቸኳይ በውጭ አገር ተካሂዶ የጋራ ብሔራዊ የትግል አጀንዳ ቀርፆ ገዥውን ክፍል ትርጉም ወዳለው ድርድር እንዲመጣ የሚያስገድድ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲቻል አሁንም ይኸ በአስቸኳይ እውን እንዲሆን ወገናዊ ጥሪያችንን ለሚመለከተው ሁሉ እናስተላልፋለን፡፡

4. ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ በኢሕአዴግ የሽብር ዘመቻ ቀን ተቀን ስቃዩን የሚያየው ሕዝባችን የመከራው ጊዜ ዘላለማዊ እንዳልሆነና መፍትኄውም በሁኔታው አስገዳጅነት ምክንያት ድርጅቶች የሚጠበቅባቸውን አመራር መስጠት አለመቻልም ይሁን በአገዛዙ አስከፊ እርምጃዎች በትግሉ ተስፋ አለመቁረጥና አገዛዙ ለሸረባቸው አንድን የሕዝብ ክፍል ከሌላው የሕዝብን ክፍል የማጋጨት እኩይና ከይሲ እቅድ ሰለባ አለመሆን ስለሆነ የተቃዋሚው ጎራ በአንድነት ሆኖ በጠራ ግንዛቤ ላይ የተመሠረቱና ተግባራዊ ለሚሆኑ ኃላፊነት የተሞላባቸው ማንኛውም ዓይነት የትግል ጥሪ ትብብርና ተሳትፎ ነቅቶ እንዲጠብቅ በትኅትናና በአክብሮት ስናሳስብ፤ በተለይ በውጭ ያለው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያዊ ተስፋ እንዲቆርጥና አንድነቱ እንዲሸርሸር አገዛዙ ለሚያደርጋቸው ዘመቻዎችም ይሁን ተራ መደለያዎች ሳይንበረከክ፥ እስካሁን ያሳየውን መሰል የሌለው አንድነቱን ጠብቆ፥ ከተቃዋሚው ጎራ የርስ በርስ አጉል ፉክቻ በመራቅና በነሱም ተስፋ ቆርጦ ከጀመረው የሕዝብና የአገር ትግል ሳይርቅ፥ ልዩነትን በማስወገድ፥ በመከባበርና በመፈቃቀር እስረኞችን ለማስፈታት ከሚደረገው ጥረት ጀምሮ ለአገራችን መሠረታዊ ችግሮች መፍትኄ ለማስገኘት በሚደረጉ የጋራ ትግል ጥሪዎች ሁሉ ተባባሪና ተሳታፊ እንዲሆን ስናሳስብ በወገናዊ አክብሮት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈለውና እየከፈለው የሚገኘውን መራር መስዋዕትነት የሚያካክስና የትግሉ ዋስትናም የጋራ ትግል ማካሄድ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ ሁሉም ወገን ለተጠናከረ፥ ሕዝባዊና አገራዊ መተክልን ለተከተለ የጋራ ትግል እንዲቆም እነሆ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል፡፡

የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ይፈቱ!

የተባበረ የሕዝብ ትግል ያሸንፋል!!

ድል  በኅብረት፥ ኅብረት ለአስተማማኝ ድል!!!

የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም